**አዋጅ ቁጥር …………/፳፻**

## በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት የዱር እንስሳት ጥበቃ፣ ልማትና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር ………….. /፳፻

በክልሉ ውስጥ አለአግባብና ዘላቂነት በሌለው አጠቃቀም ምክንያት ህልውናው አደጋ ላይ የሚገኘውን የዱር እንስሳት ሀብት በአግባቡ ማልማት፣ መጠበቅና ቀጣይነት ባለው መልኩ ጥቅም ላይ ማዋል አስፈላጊ በመሆኑ፣

የዱር እንስሳት ሀብት መጠበቅያ ክልሎችን ጠበቆ ለተተኪው ትውልድ ማስተላለፍ እንዲቻል የአካባቢው ሕብረተሰብ የጥበቃውና የልማቱ ቀጥተኛ ተሣታፊነት እና የጥቅም ተካፋይነት ወሳኝ በመሆኑ፣

በመስኩ የሚሰማሩ የግል ባለሀብቶች፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በዱር አንስሳት ጥበቃ፣ ልማትና አጠቃቀም ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ ጠቀሜታው የጎላ ስለሆነ፣

ከዱር እንስሳት ሀብት የሚገኘውን ሁለንተናዊ ጠቀሜታ (ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ሥነ-ምህዳራዊ፣ ትምህርታዊና ሣይንሳዊ) በማሳደግ ድህነትን ለመቀነስ በሚደረገው ጥረት የሚኖረውን አስተዋጽኦ ማሣደግ ተገቢ በመሆኑ፣

የክልሉን የዱር እንስሳት ሀብት ጥበቃ፣ ልማትና አጠቃቀምን የሚወስን ድንጋጌ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በዚሁ መሠረት በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ሕገመንግሥት አንቀጽ……….ንዑስ አንቀጽ……መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### ክፍል - አንድ
### ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት የዱር እንስሳት ጥበቃ፣ ልማትና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር------/፳፻ " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፣-

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

፩/ **"የዱር እነስሳት"** ማለት ከቤት እንስሳት በስተቀር በህይወት ያለ ወይም የሞተ የጀርባ አጥንት ያለው ወይም የሌለው እንስሳ ነው፤

PROCLAMATION NO------------------/2001

## A PROCLAMATION ISSUED FOR THE CONSERVATION, DEVELOPMENT AND UTILIZATION OF WILDLIFE IN THE SOUTHERN NATIONS, NATIONALITIES AND PEOPLE REGIONAL STATE

**WHERE AS**, it is necessary to develop and protect the region wildlife resources properly in a sustainable manner which is under endangered endurance due to inappropriate and unsustainable utilization;

**WHERE AS,** the direct involvement of local communities residing around a conservation area in wildlife conservation and development and utilization as well as benefit sharing thereof is essential to transfer Wildlife Protected Areas to the generation;

**WHERE AS**, it is imperative stakeholders such as governmental & non governmental organization as well as private investors to actively participate in wildlife conservation and development and utilization;

**WHERE AS**, it is necessary escalating an all round advantage (economical, social, ecological, educational, and scientific) generated from wildlife resources and there by contribute for an effort set up for the reduction of poverty;

**WHERE AS**, it has become essential to issue a provision that determines the conservation, development and utilization of the region's wildlife resources;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article-------and Sub Article---------of the Southern Nations, Nationalities and People's Regional State constitution, it is here by proclaimed as follows.

### PART-ONE
### General

### 1. Short Title

This proclamation can be referred to as "Southern Nations, Nationalities and People's regional State, Wildlife conservation, Development and Utilization proclamation Number -----/2001"

### 2. Definitions

Unless they are used under different context, the words and expressions incorporated in this proclamation shall have the following meanings.

1) "wild animals" means any live or dead vertebrate or invertebrate animal, other than domestic animal.

፪/ **“የዱር እንስሳት ሀብት”** ማለት በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የሚገኙ የዱር እንስሳት ማለት ሲሆን ከክልል ወደ ክልል እና ከአገር ወደ አገር የሚሰደዱና በጊዝያዊነት በክልሉ ውስጥ የሚኖሩትን ዝርያዎች ይጨምራል፤

፫/ **”የዱር እንስሳት ውጤት”** ማለት የማንኛውም የዱር እንስሳ ናሙና ወይም የእንስሳው አካል፣ እንቁላል፣ እጭ፣ ዝባድ፣ ቀንድ፣ ጥርስ፣ ጥፍር፣ ቆዳ፣ ሥጋ፣ ጠጉር፣ ላባ ወይም ጎፍላው ሲሆን ከእነዚህ የተሰሩ ውጤቶችንና ከእንስሳው መኖርያ አካባቢ የተገኙትን የወፍ ጎጆ፣ እንጨት፣ ሣር፣ ልጣጭ፣ አበባ፣ ማርና የመሳሰሉትን ይጨምራል፣

፬/ **”የዱር እንስሳ የመኖሪያ አካባቢ”** ማለት የየብስ፣የውሃ አካል፣ወይም ሁለቱንም የሚያካትት ሆኖ የዱር እንስሳት የሚኖሩበት የጥበቃ ቦታ ወይም ከጥበቃ ቦታ ውጪ ያለ ሥፍራን ይጨምራል፤

፭/ **”የዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታ”** ማለት ለዱር እንስሳት ጥበቃ የተከለለ ሥፍራ ሲሆን የብሔራዊ ፓርክን፣ የዱር እንስሳት ጥበቃ/ቀጠና/ክልሎችን፣ የዱር እንስሳት ቁጥጥር አደን ቀበሌዎችን፣ የዱር እንስሳት መጠለያዎችን እና የማህበረሰብ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችን ይጨምራል፤

፮/ **”ብሔራዊ ፓርክ”** ማለት የዱር እንስሳትንና ከእነዚሁ ጋር የተያያዙትን ሐይቆችንና ሌሎች በውሃ የተሸፈኑ ሥፍራዎችን ጨምሮ ለአካባቢው ውበትና ለሳይንሳዊ እውቀት የሚረዱትን የተፈጥሮ ሃብቶች ለመጠበቅ የሚከለል ቦታ ነው፤

፯/ **”የደቡብ ብሔራዊ ፓርኮች”** ማለት ሙሉ በሙሉ በደቡብ ክልል የሚገኙ ሆነው የክልሉ መንግስት የሚያስተዳድራቸውን የብሔራዊ ፓርኮችንና ለወደፊት የክልሉ መንግስት እንደ አስፈላጊነቱ ብሔራዊ ፓርክ ብሎ የሚሰይማቸውን ሥፍራዎች ይጨምራል፤

፰/ **”የዱር እንስሳት መጠለያ”** ማለት አንድ ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ ከፍተኛ ትኩረት ለተሰጣቸው የዱር እንስሳ ጥበቃ የሚከለል ሥፍራ ነው፤

፱/ **”የዱር እንስሳት ጥብቅ/ቀጠና/ ክልል”** ማለት ለዱር እንስሳት ጥበቃ የተከለለ ወይም የሚከለል ሥፍራ ሆኖ ሥፍራው ለዱር እንስሳት ጥበቃ ከመከለሉ በፊት በክልሉ ውስጥ ሰፍረው የነበሩ ሰዎች የዱር እንስሳቱን እየተንከባከቡ በቦታው እንዲኖሩ የሚፈቀድበት የጥበቃ ቦታ ነው፤

2) **“wildlife resources”** means wild animals found in the Southern Nations, Nationalities and people Region including those species migrating from Region to the region and from country to the country and temporarily staying in the Southern Nations, Nationalities and people Region

3) **“wildlife product”** means any sample of wild animal or its body part like egg, embryo, musk, horn, tooth, nail, meat, hair, feather or trophy and includes products made thereof as well as bird nest, wood, grass, flower, honey, and the like obtained from the habitat of the wildlife;

4) **“wildlife habitat”** means an area with in or out of the wildlife conservation area; in which wildlife inhabits and includes land water bodies or both

5) **“wildlife conservation areas”** means an area designated for the conservation of wildlife and includes National Wildlife Conservation Parks, Wildlife Sanctuaries, Wildlife Reserves, Wildlife Controlled Hunting Areas, and Wildlife Community Based Conservation Areas.

6) **“national park”** means an area designated to conserve, Wildlife and associated natural resources to preserve the scenic and scientific value of the area which may include lakes and other aquatic areas;

7) **“southern national parks”** means those National Parks that are found within southern region and administered by the regional government as well as those sites that will be declared as National Parks as necessary;

8) **“wildlife sanctuary”** means an area designated to conserve one or more species of wildlife that require high conservation priority;

9) **“wildlife reserve”** means an area designated to conserve wildlife where indigenous local communities are allowed to live together with and conserve the wildlife;

፲/ "የዱር እንስሳት የቁጥጥር አደን ቀበሌ" ማለት ለዱር እንስሳት ጥበቃ የሚከለልና ቁጥጥር እየተደረገ ሕጋዊ የማደን ወይም የማጥመድ ተግባር የሚካሄድበት ሥፍራ ነው፤

10) **"wildlife controlled hunting area"** means an area designated to conserve wildlife and to carry out legal controlled hunting or snaring.

፲፩/ "የአካባቢ ህብረተሰብ" ማለት በዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎች ዙርያ የሚኖሩና ውስጥ እንዲኖሩ የተፈቀደላቸውን ማህበረሰብ ያጠቃልላል፤

11) **"local community"** means people living surrounding the protected areas and those permitted to live in.

፲፪/ " ራንች" ማለት በግዥ የተገኙ ወይም ከዱር የተሰበሰቡ የዱር እንስሳትን ተንከባክቦ በማሳደግ ጥቅም ላይ ለማዋል የተከለለ ሥፍራ ነው፤

12) **"ranch"** means an area designated for the conservation and raising of purchased or collected-wildlife for latter use;

፲፫/ "የዱር እንስሳት እርባታ" ማለት የዱር እንስሳትንና የተለያዩ ውጤታቸውን እንቁላል፣ ጫጩት ወይም ግልገል በመጠቀም የማሳደግ ሥራን ያጠቃልላል፤

13) **"wildlife nurture"** means an area designated for the conservation and raising of purchased or collected-wildlife for latter use;

፲፬/ " የዱር እንስሳት ንግድ " ማለት የዱር እንስሳትንና የዱር እንስሳት ውጤቶችን ወደ ወጪ መላክ፣ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት መልሶ ወደ ውጪ መላክ ወይም እነዚህኑ የሚመለከት ማንኛውም ዓይነት የንግድ ልውውጥ ነው፤

14) **"wildlife trade"** means the import, export or re-export of wildlife or their products or any kind of business transaction related thereto;

፲፭/ "መሣሪያ" " ማለት የዱር እንስሳትን ለመግደል፣ ለመያዝ ወይም እንዳያመልጡ ለማድረግ የሚጠቀሙበት ጥይት የሚተኩስ መሣርያ፣ ዳርት ጋን፣ ተወርዋሪ ሚሳይል፣ ፈንጂ፣ ቀስት፣ ዱላ፣ ስለት፣ ወጥመድ፣ መረብ፣ መንጠቆ፣ ጉድጓድ፣ መርዝ፣ ኬሚካል፣ ወይም ሌላ ማንኛውም ለዚህ ተግባር የሚውል መገልገያ ነው፤

15) **"weapon"** means firearm, dart-gun, missile, explosives, bow and arrow, stick, sword, trap, net, hooks, holes, poison, chemical or any other instrument used to kill, capture or disable wild animals.

፲፮/ "ማደን" ማለት የዱር እንስሳትን ለመግደል፣ ለማቁሰል ለማጥፋት፣ ለማስፈራራት፣ ለማባረር፣ ለመያዝ ፣ ለማጥመድ ወይም የዱር እንስሳት ላባ ወይም ዕንቁላል ለመውሰድ የሚደረግ እርምጃ ወይም እንቅስቃሴ ነው፤

16) **"hunting"** means any measure or action taken to kill, wound, eliminate, scare, chase, capture, or trap a wild animal or taken an egg or feather of the same;

፲፯/ "የዱር እንስሳት ቁጥጥር ሠራተኛ/እስካውት/" ማለት የዱር እንስሳትና የዱር እንስሳት ውጤቶችን በሚመለከት የሚፈጸሙ ህገወጥ ድርጊቶችን እንዲቆጣጠር በሴክተሩ ወይም በሥሩ በሚገኙ መዋቅሮች/ማዕከላት ዓማካይነት የተመደበ ሠራተኛ ነው፤

17) **"wildlife anti-poaching officer"** means an officer assigned by the bureau or concerned structures/centers/ under it to control illegal acts to be committed against wildlife and wildlife products;

፲፰/ "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ወይም ማህበር ነው፤

18) **"person"** means any natural or juridical person;

፲፱/ "ፈቃድ " ማለት የልዩ ንግድ ፣ የላኪ ፣ የማደን፣ የዱር እንስሳት እርባታ፣ የዱር እንስሳት ራንች ፈቃድ እና የባሌቤትነት ፈቃድ ማለት ነው፤

19) "license" means licenses for special trade, export, hunting, wild animals raising or ranch and ownership.

፳/ ”ባለስልጣን” ማለት የኢትዮጵያ ፌደራል ዲሞክራሲያዊ መንግስት የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ባለስልጣን ማለት ነው፣

፳፩/ ”ክልል መንግስት” ማለት የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት ነው፣

፳፪/ ”ክልል” ማለት በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት የሚተዳደሩ ቦታዎች በሙሉ ነው፣

፳፫/ **”ቢሮ”** ማለት የደቡብ ብሔሮች ፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት የንግድና ኢንዱስትሪ ሴክተር ነው፤

**፫. ዓላማ**

የዚህ አዋጅ ዋና ዋና ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው

፩/ የክልሉን የዱር እንስሳት ሀብት ለመጠበቅ፣ ለመንከባከብ፣ ለማልማትና በአግባቡ ጥቅም ላይ ለማዋል፤

፪/ በዱር እንስሳት ሀብት ላይ የተመሠረተ የቱሪዝም እንቅስቃሴ እንዲስፋፋና በመስኩ የግል ባለሀብቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ፣

፫/ በክልሉ የዱር እንስሳት ሀብት የአካባቢ ህብረተሰብ ክልሉ እና ሃገሪቱ ዘላቂ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታዎች ለማመቻቸት።

**ክፍል ሁለት**

**የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች**
**እና የህጋዊ አደን እንቅስቃሴዎች**

**፬. በክልል መንግስት የሚሰየሙና የሚተዳደሩ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች**

፩/ የሚከተሉት የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች በክልሉ መንግስት የሚሰየሙና የሚተዳደሩ ይሆናሉ፡

ሀ) ከፍተኛ የዱር እንስሳት ብዝሀ-ሕይወት ስብጥርና ተፈጥሮአዊ ውበት ኖሯቸው አካባቢያዊ፣ አገር አቀፋዊና ዓለም ዓቀፋዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ወካይ ምህዳረ ቀጠናዎችን የያዙ የክልሉን ብሔራዊ ፓርኮች፣ የዱር እንስሳት ጥብቅ ክልሎች፣ የዱር እንስሳት የቁጥጥር አደን ቀበሌዎችንና የዱር እንስሳት መጠለያዎችን ያጠቃልላል፤

ለ) በመልክአ ምድር አቀማመጣቸው በሁለትና ከዚያም በላይ ባሉ ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች አስተዳደር የሚገኙ ማናቸውም የዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎች፣

20) “authority” means the Ethiopia federal democratic government wildlife conservation, development and utilization Authority.

21) “regional government” refers to the Southern Nations, Nationalities and Peoples’ Regional Government.

22) “region” refers all the areas administered by the Southern Nations, Nationalities and Peoples’ Regional Government.

23) “bureau” means the regional trade and industry bureau

**3. Objective**

This proclamation shall have the following objectives:

1. to conserve, manage, develop and properly utilize the wildlife resources of the region;
2. to expand wildlife-based tourism activities and enhance the involvement of private investors thereto;
3. by creating conducive situation to ensure the sustainable benefits of the region wildlife recourses to the local community, the region and the country all together

PART TWO

WILDLIFE CONSERVATION AREAS
AND HUNTING ACTIVITIES

**4. Wildlife Conservation Areas to be Designated and Administered by the Regional Government**

1/ the following wildlife conservation areas shall be designated and administered by the regional government:

A) national parks, wildlife reserve, wildlife controlled hunting areas and wildlife sanctuaries that are locally, nationally and globally significant and known to have representative ecological zones and embrace immense diversity of wildlife and natural scenery;

B) any wildlife conservation areas geographically situated within two or more zonal or special werdas administrations;

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱት የዱር እንስሳት ቦታዎች የሚሰየሙት ቢሮው በሚያቀርበው ሀሳብ መሰረት የክልሉ ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይሆናል፡፡

**፭. በአካባቢ ሕብረተሰብ የሚተዳደሩ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ (፬) ከተመለከቱት የጥበቃ ቦታዎች ውጪ የሚገኙ የዱር እንስሳት መኖርያ አካባቢዎች በአካባቢው ህብረተሰብ እንዲተዳደሩ ቢሮው ሊፈቅድ ይችላል፡፡

**፮. በግል ባለሀብቶች የሚተዳደሩ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች፡**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ (፬) የተመለከቱትን የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች የክልሉ መንግስት ከፌደራል መንግስትና ከግል ባለሀብቶች ጋር በሚያደርጓቸው የሶስትዮሽ የኮንሴንሽን ውሎች መሠረት የግል ባለሀብቶች እንዲያስተዳድሩ ሊፈቀድላቸው ይችላል፡፡

**፯. የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችን መሰየም፣ መከለልና መመዝገብ**

፩/ ቢሮው አዳዲስ የዱር እንስሳት መኖሪያ አካባቢዎችን አግባብ ካላቸው አካላት ጋር ሆኖ በማስጠናት በተለያዩ የጥበቃ ቦታዎች አይነት እንዲሰየሙ፣ እንዲከለሉና እንዲቋቋሙ ለክልሉ መንግስት ያቀርባል፣

፪/ ቢሮው በዚህ አዋጅ አንቀጽ (፬) የተመለከቱትን ነባር የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችን ከሚመለከታቸው መንግስታዊ አካላትና ከአካባቢ ህብረተሰብ ጋር ተቀናጅቶ በማጥናት እንደገና የማካለልና ህጋዊ መሠረት እንዲኖራቸው ያደርጋል፣

፫/ ቢሮው ከዞኖችና ከልዩ ወረዳዎች አስተዳደር እንዲሁም ከአካባቢ ህብረተሰብ ጋር በመሆን በአካባቢ ህብረተሰብ የሚተዳደሩ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችን ያጠናል፣ እንዲከለሉና እንዲቋቋሙ ያደርጋል፤ .

፬/ ቢሮው አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመሆን የዱር እንስሳት ሀብት የሚጠበቁበትና በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ራንቾችንና ሌሎች መዋዕለ እንስሳት እንዲቋቋም ያደርጋል፣

፭/ ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፣ (፪) እና (፫) የተመለከቱትን የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች የማቋቋምያና የማስፈጸምያ ደንቦችን ያዘጋጃል፣ ለክልሉ መንግስት በማቅረብ ሲጸድቅ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣

2/ The wildlife conservation areas referred to in Sub-Article (1) of this Article shall be designated by regulations to be issued by the council of the regional government upon the recommendation of the Bureau

**5. Wildlife conservation areas to be administrated by local communities**

Wildlife habitats other than the conservation areas referred to in article (4) of this proclamation may be endorsed by the bureau to be administered by the local communities

**6. Wildlife conservation areas to be administrated by private investors**

Private investor may be sanctioned to administer the Wildlife conservation areas referred to in Article (4) of this proclamation based on trilateral concession agreements concluded between the private investor, Federal and the Regional Governments.

**7. Naming, reserving and registering wildlife conservation areas**

1) The bureau investigate new wildlife habitats with concerned organs and propose to the regional government for naming, reserving and establishment;

2) The existing Wildlife conservation areas referred to in Article (4) of this proclamation investigated for re-demarcation and to have legal basis by the bureau in collaboration with concerned governmental bodies and local communities ;

3) The bureau with zonal and special woredas administrations as well as local communities investigate, demarcate and establish Wildlife conservation areas that are administered by local communities;

4) The bureau in collaboration with appropriate bodies/organs have the responsibility to establish ranches or other zoological gardens for wildlife conservation and proper utilization;

5) The Bureau has the responsibility to prepare establishment and execution regulations of wildlife conservation areas referred to in Sub-Article (1), (2) and (3) of this Article and submitted to the regional government; upon approval follow up implementations.

፮/ ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፣ (፪) ፣ (፫)እና (፬) የተመለከቱትን የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች የማስፈጸምያ መመሪያዎችን በማዘጋጀት ተግባራዊነቱን ይከታተላል::

**፰ የአደን ፈቃድ**

፩/ ማንኛውም ሰው ከሚመለከተው <u>የፌደራል ባለስልጣን</u> ወይም የክልሉ ቢሮ ፈቃድ ሳይዝ የዱር እንስሳት ማደን የተከለከለ ነው፣

፪/ የአደን ፈቃድ የሚሰጥበት፣ የሚታደስበት፣ የሚታገድበትና የሚሰረዝበት ሁኔታ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት የሚወሰን ይሆናል፣፡

፫/ ቢሮው በክልል ደረጃ የአደንና የአደን ዘዴዎችን በሚመለከት ደንብና መመሪያ ያዘጋጃል ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

**፱ ለሳይንሳዊ ተግባር የዱር እንስሳትን ወይም ውጤቶቻቸውን የመሰብሰብ ፈቃድ**

፩/ ከታወቀ የሳይንስ ተቋም የተጻፈ የድጋፍ ደብዳቤ በመያዝ የዱር እንስሳት ወይም ውጤት ለመሰብሰብና ለሳይንሳዊ ተግባር ወይም ትምህርት ለማዋል ለሚጠይቅ አመልካች እንደ አስፈላጊነቱ የክልሉ ቢሮ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፣

፪/ ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን ፈቃድ የሚሰጠው ከዚህ አዋጅና የዱር እንስሳት ጥበቃን ከሚመለከቱ ሌሎች ህጎችና ደንቦች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይሆናል፡፡

## ክፍል ሦስት
## ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎችና ጥቅሞች

**፲ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ**

፩/ በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታ ውስጥ የሚደረግ ማንኛውም ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ የዚህን አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎችን በማይቃረን ሁኔታ መካሄድ አለበት::

፪/ ሴክተሩ በሥሩ የሚተዳደሩ የብሔራዊ ፓርኮችንና የሌሎች የዱር እንስሳት መጠበቅያ ስፍራዎችን የተለያዩ ገቢዎች በአንድ የባንክ ሂሳብ ቋት ይሰበስባል::

6) The Bureau has the responsibility to prepare execution directions of wildlife conservation areas referred to in Sub-Article (1), (2), (3) and (4) of this Article and follow up its implementations.

**8. Hunting permit**

1) Wild animal hunting is forbidden for any person unless he is in possession of hunting permit from concerned federal wildlife authority or the region bureau;

2) The conditions applicable for the granting, renewal, suspension and revocation of hunting permits shall be determined by regulations and directives issued under this proclamation.

3) The bureau shall issue regulations pertaining to appropriate hunting and hunting methods.

9. **Permit for Collection of Wildlife or Wildlife Products for Scientific Purposes**

1. The Region bureau may grant permit to an applicant in possessions of recommendation letter from a recognized scientific institution for collecting wildlife or their products for scientific purpose.

2. The Bureau shall grant the permit referred to in Sub-Article (1) of this Article in accordance with directives issued by it in conformity with the provisions of this proclamation and other laws and regulations pertaining to wildlife conservation

## PART THREE
## ECONOMIC ACTIVITIES AND BENEFITS

10. Economic activities

1/ Any economic activity to be undertaken within a wildlife conservation area shall be carried out in accordance with this proclamation and regulations and directives to be issued hereunder.

2/ The bureau shall collect all revenue generated in national Parks or other wildlife conservation areas administered under it in one account.

፫/ በአካባቢ ህብረተሰብ የሚተዳደሩ የጥበቃ ቦታዎችን የገቢ አሰባሰብ በተመለከተ የክልሉ መንግስት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በሚያወጣው የዱር እንስሰሳት የገቢ አጠቃቀምና ክፍፍል ደንብ መሠረት የሚወሰን ይሆናል::

፬/ ከዱር እንስሳት ሃበት የሚገኘውን የተለያዩ ገቢዎች የጥበቃ ቦታዎች ባለድርሻዎች ዞኖች፣ ልዩወረዳዎች፣ ወረዳዎች፣ የአካባቢው ሕብረተሰብ እና የጥበቃ ቦታዎች እንዲሁም ሴክተሩ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፤

፭/ ሴክተሩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪)፣ (፫) እና (፬) የተመለከቱትን የዱር እንስሳት ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ደንቦችን በማዘጋጀት ለክልሉ መንግስት ያቀርባል፣ ሲፈቀዱም ተግባር ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤

፮/ ሴክተሩ የዱር እንስሳት ገቢ አሰባበሰብና አጠቃቀምን በተመለከተ የማስፈጸምያ መመሪያዎችን በማዘጋጀት ተግባራዊነቱን ይከታተላል፡፡

**፲፩/ በዱር እንስሳት ሀብት ላይ የተመሠረተ ቱሪዝም**

፩/ ሴክተሩ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በዱር እንስሳት ሀብት ላይ የተመሠረቱ የቱሪዝም ኢንቨስትሜንቶችን ያበረታታል::

፪/ ሴክተሩ ዞኖች፣ ልዩ-ወረዳዎች እና ሌሎች የሚመለከታቸው በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ውስጥም ሆነ ከእነሱ ውጪ የሚከናወኑ የኢኮቱሪዝም ልማት አካባቢውን የጠበቀ እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡

**፲፪/ በዱር እንስሳትና ውጤቶቻቸው ስለመነገድ**

፩/ እንደ አግባቡ ከፌደራል የባለስልጣን ወይም ከሚመለከተው የክልል ቢሮ በተገኘ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር፣

ሀ/ በዱር እንስሳትና በዱር እንስሳት ውጤቶች የመነገድ ተግባር ማካሄድ፣

ለ/ ማንኛውም የተዘጋጀ ወይም ያልተዘጋጀ የዱር እነስሳት ውጤት በባለቤትነት መያዝ ወይም መሸጥ፣ማስተላለፍ፣ ከቦታ ወደ ቦታ ማስተላለፍ የተከለከለ ነው፡፡

3/ the revenue collection of conservation areas administered by local communities shall be determined by the revenue utilization and share regulation set to implement this proclamation by the regional government.

4/ Stakeholders of conservation areas including zones, special-weredas, weredas, local communities and conservation areas as well as the bureau shall be benefited from the different revenue collected from wildlife resources.

5/ The Bureau have the responsibility to prepare and present to the regional government wildlife revenue collection and utilization regulations referred to in Sub-Article (2), (3) and (4) of this Article and submitted to the regional government; and follow up the implementation of the same upon approval.

5/ The Bureau have the responsibility to prepare execution directives of wildlife revenue collection and utilization and follow up its implementations.

**11. Wildlife Resource Based Tourism**

1/ The bureau shall, in collaboration with the relevant bodies, promote investment in wildlife-based tourism.

2/ the regional bureau, zones, especial woredas and other concerned bodies, shall ensure that eco-tourism development activities to be undertaken in or outside of wildlife conservation areas shall be carried out environmentally friendly.

**12. Trading in wildlife and their products**

1/ the following are prohibited unless a permit is obtained from the Federal Authority or the concerned regional bureau, as appropriate:

a) Any activity of trade in wildlife and their products;

b) The owner ship, sale, transfer, export or import of any processed or unprocessed wildlife product.

## ክፍል- አራት
## ልዩልዩ ድንጋጌዎች

### ፲፫ የተከለከሉ ተግባሮች

፩/ ማንኛውም ሰው

ሀ) አግባብ ካለው የፌደራል ባለስልጣን ወይም ከክልሉ ሴክተር ካልተፈቀደለት በስተቀር በዱር እንስሳት የጥበቃ ክልል ውስጥ ወይም ወጪ የዱር እንስሳት አደን ማካሄድ የተከለከለ ነው፣

ለ) በዱር እንስሳት የጥበቃ ክልል ውስጥ ህገወጥ የዱር እንስሳት አድን፣ ዓሳ ማስገር፣ ሰደድ እሳት መልቀቅ፣ ደን መመንጠር፣ የጦር መሣሪያ ወይም መርዛም ንጥረ ነገሮችን ይዞ መግባት፣ ሰፈራዎችን ማካሄድ፣ የቤት እንስሳት ግጦሽና እርሻ ማካሄድ፣ የንብ ቀፎ መስቀል ወይም ተመሳሳይ ተግባሮች ማካሄድ የተከለከለ ነው፣

፪/ በክልሉ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የማዕድን ሥራ፣ የመንገድ ሥራ፣የውሃ ቁፋሮ የመሳሰሉት ተግባሮች ለማካሄድ ወይም እነዚህኑ በተመለከተ የሥራ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት አግባብ ያለው የክልሉ አካል ከቢሮው ጋር ስምምነት መደረስ አለበት፣

፫/ ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት ከዱር እንስሳትና የዱር እንስሳት ውጤቶች ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መልኩ ተያያዥነት ባላቸው የሥራ መስኮች ያለህጋዊ ፈቃድ መሰማራት አይችልም፡፡

### ፲፬. የክልሉ ሴክተር ሥልጣንና ተግባር

የክልሉ ቢሮ በዚህ አዋጅ በሌሎች ድንጋጌዎች ከተሰጡት በተጨማሪ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡

፩/ የክልሉን የዱር እንስሳት ሀብት ጥበቃ፣ ልማትና አጠቃቀምን ፕሮግራም ያዘጋጃል ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ (፬) መሠረት የተቋቋሙትን የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችን ያለማል ያስተዳድራል፣ ሕገወጥ ተግባራት እንዳይፈጸሙባቸው ይከላከላል፣

፫/ ለሀገር ውስጥ ቱሪስቶች የአድን ፈቃድ ይሰጣል፣

፬/ ለአሳዳኝ ድርጅቶች የማሳደን መብት ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል ቁጥጥርና ክትትል ያደርጋል

## PART FOUR
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 13. Forbidden activities

1/ No person

A) Can hunt in and outside conservation areas unless he obtain permission from concerned federal wildlife authority or the region bureau; as appropriate

B) Can carryout illegal hunting, fishing, set fire, clearing vegetation, taking firearms and poisons chemicals, settlement, domestic animals grazing, cultivation, hanging beehives and other similar practices are forbidden in wildlife conservation areas.

2/ There shall be common agreement of the authorized regional body with the bureau before giving work permits to carry out mining, road construction, water-well digging and other similar practices with in the Region wildlife conservation areas.

3/ No person or organization can directly or indirectly engage in filed of business related to wildlife and their products without having legal permission.

### 14. Power and responsibilities of the Region Bureau

The bureau shall, in addition to those given to it under other provisions of thi proclamation, have the powers and responsibilities to :

1/ prepare the region wildlife resources conservation, development and utilization program and follows up its implementation;

2/ develop and administer wildlife conservation areas established in accordance with article 4 of this proclamation and control illegal activities to be committed in relation thereto;

3/ issue hunting permits for domestic tourists;

4/ issue the right of hunting license for hunting safaris renew license and control and follow up their activities

፭/ የዱር እንስሳት ጥበቃ፣ ልማትና አጠቃቀምን በሚመለከት ጥናትና ሥልጠና ያካሂዳል፣ ወቅታዊ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያቀናብራል፣ ለተጠቃሚዎች ያሠራጫል፣

፮/ በሚያስተዳድራቸው የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችና ከዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ውጪ የሚገኙት የዱር እንስሳት ሕገ ወጥ ተግባራት እንዳይፈጸሙባቸው ክትትል ያደርጋል፣

፯/ በግል ባለሀብቶችና በአካባቢ ሕብረተሰብ የሚተዳደሩትን የዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎችን ይቆጣጠራል፣ እንደአስፈላጊነቱ ድጋፍና ትብብር ያደርጋል፤

፰/ በዱር እነስሳት ጥበቃ ቦታዎችም ሆነ ከጥበቃ ቦታዎች ወጪ በሚገኙ የዱር እንስሳት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ በሽታዎችን ይከላከላል፣ ከአቅም በላይ ሲሆን ከፌደራሉ የባለስልጣን መ/ቤት ድጋፍ ይጠይቃል፣

፱/ የዱር እንስሳት እርባታና ራንች ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ አፈጻጸማቸውን ይቆጣጠራል፣

፲/ በሰው ሕይወትና ንብረት ላይ አደጋ በሚያደርሱ የዱር እንስሳት ላይ ተገቢውን ጥናት በማካሄድ ችግሩ የሚቃለልበትንና የሚወገድበትን እርምጃ ይወስዳል፣ ከአቅም በላይ ሲሆን ለባለስልጣኑ በማሳወቅ ድጋፍና መፍትሔ ይቀይሳል፣

፲፩/ የዱር እንስሳትና የዱር እንስሳት ውጤቶች በባለቤትነት ለመያዝ፣ ለማስተላለፍና በአገር ውስት ለመሸጥ የሚያስችል ፈቃድ ይሰጣል፡፡

፲፪/ በክልሉ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ውስጥ ለሚገነቡ የቱሪስት አግግሎት መስጫ ተቋማት( ሎጅ፣) የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል፣ ቅድመ አካባቢያዊ ተጽዕኖ ጥናት ያካሂዳል፤

፲፫/ በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ውስጥም ሆነ ወጪ የሚገኙ ሀገሪቱ በብቸኝነት የምትታወቅባቸውን እንዲሁም ሌሎች በመመናመን ላይ ለሚገኙ የዱር እንስሳት ዝርያዎቸ ልዩ ትኩረት በመስጠት የሚመለከታቸው አካላትን በማስተባበር ለማጥናትና ለመንከባከብ የሚያስችል አሰራር ይዘረጋል፤

፲፬/ የዱር እንስሳት ጥበቃ፣ ልማትና አጠቃቀም በተመለከተ የአካባቢውን ህብረተሰብ ግንዛቤ ከማሳደግ አኳያ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የተቀናጀ ሥራ ይሰራል።

፲፭/ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚረዱ ደንቦችንና መመሪያዎችን ሊያዘጋጅ ይችላል።

## ፲፮. የዞንና የልዩ ወረዳዎች ሥልጣንና ተግባር

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ (፬) የተመለከቱትን የጥበቃ ቦታዎችን ህልውና ጠብቆ ለማቆየት እንዲቻል ከክልሉ ሴክተር ጋር በመቀናጀት ለዱር እንስሳት ጥበቃና ልማት ሥራዎች ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋሉ፤

፪/ በአካባቢያቸው በሚገኙ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችና ከዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ውጪ በሚገኙ ዱር እንስሳት ላይ ሕገ ወጥ ተግባራት እንዳይፈጸምባቸው ይከላከላሉ፣ የዚህ አዋጅ ደንብና መመሪያ በሚፈቅደው መሠረት በህገወጦች ላይ ተገቢውን ህጋዊ እርምጃ ይወስዳሉ፣

፫/ በአካባቢያቸው በግል ባለሀብቶችና በአካባቢ ሕብረተሰብ ለሚተዳደሩ የዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎች የተለያዩ ድጋፎችን ያደርጋሉ።

## ፲፯. የዱር እንስሳት ቁጥጥር ሠራተኛ (ስካውት) ሥልጣንና ተግባር

የዱር እንስሳት ቁጥጥር ሠራተኛ የሚከተለው ሥልጣን ይኖረዋል፡

፩/ የዱር እንስሳት ወይም የዱር እንስሳት ውጤት ይዞ የተገኘውን ማንኛውንም ሰው እንዚህኑ ለመያዝ ያስቻለውን ሕጋዊ ፈቃድ እንዲያሳይ የመጠየቅ፣

፪/ ሕግን በመተላለፍ በይዞታ ሥር የተደረጉ የዱር እንስሳት ወይም የዱር እንስሳት ውጤቶች ተደብቀዋል ብሎ ለማመን በቂ ምክንያት ሲኖር ያለፍርድ ቤት ማዘዣ ወደ ማንኛውም ሰው መሬት፣ ህንጻ፣ድንኳን፣ ተሽከርካሪ፣ የአየር መንኮራኩር ወይም ጀልባ ውስጥ የመግባትና የመፈተሽ እንዲሁም ሻንጣ ወይም እሽግ የመበርበር፣

፫/ ሕግን በመተላለፍ በይዞታ ሥር የተደረጉ የዱር እንስሳትና የዱር እንስሳት ውጤቶችን እንዲሁም ጥፋት የተፈጸመባቸውን መሣሪያዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፭/፪ መሠረት እንዲወረሱ ለማድረግ እንዲቻል በቁጥጥር ሥር የማድረግና የክልል ሴክተር ባወጣው የመመዝገቢያ ቅጽ መሠረት ተገቢውን ደረሰኝ ሰጥቶ የመረከብ፣

፱/ የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፲፰ ድንጋጌዎች በመተላለፍ ጥፋት ሲፈጽም ያገኘውን ሰው ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ይዞ ለሚመለከተው ህግ አስከባሪ አካል ማቅረብ፣

## ፲፯. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ይህንን አዋጅና በአዋጁ መሠረት የሚወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን በማስፈጸም ረገድ አግባብ ካለው አካል ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

## ፲፰ ቅጣት

፩/ ይህንን አዋጅ ወይም ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚወጡትን ደንቦችና መመሪያዎችን የሚተላለፍ በወንጀልኛ መቅጫ ሕግ መሰረት የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር፡

ሀ/ ማንኛውም ሰው

i. ሕገወጥ የዱር እንስሳት አደን ወይም ንግድ ድርጊትከፈጸመ፣

ii. በዚህ አዋጅ አንቀጽ (፲፫) **ንዑስ አንቀጽ** (፩) ና (፪) የተመለከቱትን የተከለከሉ ተግባሮችን ካከናወነ ወይም በማናቸውም አኳኋን በነዚሁ ላይ ጉዳት ካደረሰ፣

iii. የዱር እንስሳትን ወይም የዱር እንስሳት ውጤቶችን ያለፍቃድ ይዞ ከተገኘ፣

ከብር ፳ሺ በማያንስና ከብር ፴ሺ በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአንድ ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

ለ/ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም አዋጁን ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን በመተላለፍ ሌሎች ጥፋቶችን የፈጸመ ማንኛውም ሰው ከብር ፳፻ በማያንስና ከብር ፫ሺ በማይልጥ መቀጮ ወይም ከአንድ ወር በማያንስና ከስድስት ወር በማይበልጥ እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ፍርድ ቤት ቅጣት ሲወስን ከቅጣቱ በተጨማሪ ከጥፋቱ የተገኘው የዱር እንስሳ ወይም የዱር እንስሳ ውጤት እንዲሁም ጥፋቱ የተፈጸመበት መሣሪያ ውርስ እንዲሆን ይወሰናል፡፡

፫/ ሴክተሩ ወይም በሴክተሩ ሕጋዊ ውክልና ወይም ስልጣን የተሰጠው አካል የተወረሰውን የዱር እንስሳ ወይም የዱር እንስሳ ውጤት እንዲሁም (ከጦር መሣሪያ በስተቀር ጥፋቱ የተፈጸመበት መሣሪያን እንደአግባቡ መሸጥ፣ ለሳይንስ ተግባር፣ ለትምህርት

ተቋማት ማስተላለፍ ወይም ከጥቅም ውጪ ማድረግ ይችላል፡፡

## ፲፱. ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

፩/ የክልሉ ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ሴክተሩ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፫/ የሚከተሉተ ደንቦች በዚህ አዋጅ መሠረት እንደወጡ ተቆጥረው የጸኑ ይሆናሉ፣

ሀ/ የማዜና ጨበራ ጨርጨራ ብሔራዊ የዱር እንስሳት ጥበቃ ፓርኮች ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፺፪/፲፱፺፯፣

ለ/ የክክልሉ የቱሪስት መሰህቦች የገቢ አጠቃቀም ደንብ ቁጥር-----/፳፻ ፡፡

## ፳. ተፈጻሚ ስለማይሆኑ ሕጎች

ይህን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያና ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑት ሕጎች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## ፳፩. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከፀደቀበት ከ………………….ቀን ፳፻፩ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ሽፈራው ሽጉጤ

የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ርዕሰ መስተዳድር